# የእንቦጭ አረም ማስወገጃ ማሽን ሀገር ውስጥ ገባ

February 11, 2018



ማሽኑ በሰዓት 5ሺህ ካሬ ሜትር የማስወገድ አቅም አለው፡፡

በጣና ላይ የተዛመተውን የእንቦጭ አረም ለማስወገድ የሚያስችል ዘመናዊ ማሽን ሀገር ውስጥ ገብቷል፡፡

ባህር ዳር ሲገባም አቀባበል ተደርጎለታል፡፡

የአረም ማስወገጃ ማሽኑን ገዝቶ ለክልሉ መንግስት ያስረከበው በባህር ዳር የተቋቋመው አማጋ የስፖንጅ ውጤቶች ማምረቻ ድርጅት ነው፡፡

የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ አቶ ገብሩ ምትኩ እንዳሉት ማሽኑ በሰዓት 5ሺህ ካሬ ሜትር የማስወገድ አቅም አለው፡፡

በቅርቡም ከውጭ ሀገር በሚመጡ ባለሙያዎች ተገጣጥሞ ለሀገር ውስጥ ሙያተኞች ስልጠና በመስጠት ወደ ስራ ይገባል ብለዋል፡፡

የአማራ ክልል አካባቢ ደንና ዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ዶክተር በላይነህ አየለ ማሽኑን ለገዛው አማጋ የስፖንጅ ውጤቶች ማምረቻ ድርጅት ምስጋና አቅርበዋል፡፡

በቀጣይም ባለሀብቱንና በጎ አድራጎት ማህበራትን በማስተባበር በጣና ላይ የተጋረጠውን አረም የማስወገድ ተግባር በስፋት ይከናወናል ብለዋል፡፡

የእንቦጭ አረምን ለማስወገድ በሚደረገው ዘመቻ መንግስት ከቀረጥ ነጻ ማሽኖች እንዲገቡ ከማድረግ ጀምሮ ልዩ ልዩ ድጋፎችን የማድረግ ስራውን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ያረጋገጡት ደግሞ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳደር ጽ/ቤት ሀላፊ አቶ ያየህ ሀዲስ ናቸው፡፡

የአረም ማስወገጃ ማሽኑ ባህር ዳር ሲገባ አቀባበል ተደርጎለት ወደ ጎርጎራ መሸኘቱን የዘገበው ስማቸው እሸቴ ነው፡፡